# ያቺን ዕለት ባሰብኳት ጊዜ

/ከፈቀደ ጌታ /

የድሃ ልጅ ነኝ፡፡እናቴ እኔን ያሳደገችኝ 'አፈር ግጣ' ነው፡፡ለእናት ብቸኛ ሆኖ ያለረዳት ልጅን ማሳደግ ምንኛ ከባድ እንደሆነ ለማወቅ እኔን ጠይቁኝ፡፡የእናቴን እንቅልፍ አልባ ልፋት ባውቀውም ተማሪ ነኝና አንዳች ጠብ የሚል ነገር ከእጄ አውጥቼ "እንቺ በዚህች ገንዘብ ይህቺን ነገር ግዢ 'ልላት አልቻልኩም፡፡የምታቀርብልኝን ስበላ እንባዬ እየመጣብኝ ነው፡፡ቁጭ ብዬ የምበላው ላቧንና የጉልበቷን መቅኔ መሆኑን ሳስብ ይተናነቀኛል፡፡ጠላ ጠምቆ በሳምንት ለመሸጥ ከሰኞ እስከሰኞ ያለባትን ልፋት ሳስበው " እንዴት ያለችው ጠንካራ ሴት ናት" እላለሁ ለራሴ፡፡የእሷ ተስፋ ደግሞ እኔ ላይ ተንጠልጥሎ ቀርቷል፡፡እድሜ ብቻ ሳይሆን ከአቅም በላይ የሆነ ድካምና ሃሳብም ተሸክማ ኖራለችና በቶሎ መድከሟ አይቀርም፡፡ለዓመታት ያለእረፍት የለፋችበት እጇ መዛሉ፣ እንስራ ተሸክማ የኖረችበት ወገቧ መጉበጡም አይቀርም፡፡ያኔ አቅም ያንሳታል ፣እንደዛሬው እንስራ አገላብጣ ማጠብ፣ጌሾ አድቅቃ መውቀጥ፣ 50 ኪሎ በቆሎ ቆልቶ ማስፈጨትና ተሸክሞ መምጣት አትችልም፡፡ይህን ስታስብ ይመስለኛል " ያኔ ይህን ልጄን ምን ይውጠው ይሆን " ብላ በጭንቀት የምትሰቃየው፡፡ ከዛሬው ማጣቷና ድካሟ ይልቅ የእኔ የወደፊት እጣ ነው ይበልጥ በሽታ የሆነባት፡፡

ቅድመ 1983

እናቴን ምን ላድርጋት? አልንገራት እንጂ ባየኋት ቁጥር ልቤ በሃዘን ይጠይማል፡፡ልክ እንደሷ እኔም ወደፊት ተስፋ አይታየኝም፡፡ደሃ ሆኜ ተፈጥሬ ደሃ ሆኜ መሞት አልፈልግም፡፡ከፍ እያልኩ ስሄድ ልረዳት የቻልኩት ነገር ቢኖር ወፍጮ ቤት የተቆላ በቆሎ ተሸክሜ መሄድና አስፈጭቼ መምጣት፣እንስራ ሙሉ ውሃ ተሸክማ ስትመጣ ከወገቧ ላይ ለማውረድ ማገዝ ብቻ ሆነ፡፡ይህንን ደግሞ ለኔ የምትሰስተው እናቴ አትፈልገውም፡፡እስከማሟጠጫ ጉልበቷ ድረስ ሁሉን ነገር ራሷ ሰርታ እኔን ግን ለጥናት ጊዜ እንዲኖረኝ ማድረግ ብቻ ነው የምትሻው፡፡አንዳችን የአንዳችንን የስሜት ስቃይ እያየን መኖሩ ህመም ሆኖብናል፡፡

እኔ ምን ላድርግ፡፡የምኖረው ለኔ ብጤ ወጣቶች አማራጭ በሌለበት ዘመን ነው፡፡ የምማረውን ትምህርት አጥብቄ ለመያዝ ብሞክርም ሃሳቤ ግን በኑሮ ጫና እና በውትድርና ፍራቻ ተከፋፍሎ ውጤቴ ላይ ተጽዕኖ እያሳረፈብኝ ነው፡፡ከትምህርቴ ጠብ የሚል እውቀት ማካበት አልቻልኩም፡፡መምህራኑ ፖለቲካ፣ቅይጥ ኢኮኖሚ፣የእንጨት ስራ ወዘተ እየተባለ በየጊዜው ተደበላልቆ የሚመጣውን ትምህርት በጭንቅላቴ ሲሰገስጉብኝ ውዬ ማታ ራሴን እጠይቀዋለሁ፡፡እውን ይሄ እውቀት ነው እናቴን ከጠላ መሸጥ አውጥቶ የበሰለ እንጀራ እንድትበላ የሚያስችላት?እላለሁ፡፡ከድህነት የሚያላቅቀኝ አንዳች እውቀት ወይም የወደፊት ህይወቴን የሚቀርጽልኝ አንዳች ሙያ በውስጤ አለመግባቱን ስረዳ ተስፋ እቆርጣለሁ፡፡

እንዲያም ሆኖ ጠላ ጠጪዎች እየተንጫጩብኝም ቢሆን አንዲት ጥግ ላይ መደብ ይገፍ ለማጥናት የሚሆን ጥንካሬ አላጣሁም፡፡ያኔ የለመደብኝ ነው መሰል ዛሬም ድረስ በጸጥታ ውስጥ ማጥናት አልችልም፡፡ምኞቴ ለጊዜው የእናቴን ተስፋ ማለምለም ብቻ ነው፡፡ያለሁበትን ዘመን ሳስበው ግን ለዚያ ምኞት ስኬት የሚያበቃኝ አንዳች መንገድ አልታየኝ ብሏል፡፡ከትናንት ዛሬ አልሻል ሲልብኝ ነገን ማመን አልቻልኩም፡፡

ቁመቴ እየረዘመ ፣እድሜዬም እየጨመረ ሲሄድ ደግሞ በድህነቴ ላይ ሌላ ጣጣ መጣብኝ፡፡ያለችኝን ሙጣጭ ተስፋ የሚያሳጣኝ ጣጣ፡፡በቡሃ ላይ ቆረቆር እንዲሉ ፡፡የቀበሌ አብዮት ጥበቃ ዓይን ይከተለኝ ጀመር፡፡እናቴ ተሳቀቀች፡፡"እባክህ ጎንበስ ብለህ ሂድ መርዘምህን አይተው እንዳያዘምቱብኝ" ትለኛለች ሁሌ፡፡ ደርግ ከዚህም ከዚያም ራሱ በፈጠራቸው ችግሮች ተወጥሮ መላወሻ ባጣበት በዚያን ጊዜ አጠገቡ ያለውን ቀርቶ ራሱንም ማመን እንደተሳነው የተረዳሁት በአንድ አስቂኝ አጋጣሚ ነው፡፡

የምኖርበት ቀበሌ አብዮት ጥበቃ ጽህፈት ቤት እኔን ...አንድ ከምንም የማልጣፍ የ16 ዓመት ታዳጊ ህጻንን ... እቅድ አውጥቶ "በጸረ አብዮተኝነት" ይከታተለኝ እንደነበር ስረዳ በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ፡፡ያኔ ማታ ማታ የቤታቸን ብቸኛ ሃብት በሆነችው ራዲዮ እየተባባሰ የመጣውን ጦርነትና ውጤቱን  ለመስማት የውጭ ሃገር የአማርኛ ስርጭቶችን ጣቢያ ስጎረጉር አመሻለሁ፡፡ያቺ ራዲዮ አቅም አንሷት ነው መሰል የምፈልገውን ወሬ ስባ ልታመጣልኝ አልቻለችም፡፡ቢቸግረኝ በአንዲት የአጥር ሽቦ አንቴና ሰራሁና እድሜ ያዛገው የጣራችን ቆርቆሮ ላይ አሰርኳት፡፡አንቴናዋን አፈሩ ረግፎ ንፋስ በሚያስገባው ግድግዳችን በኩል አሳልፌ ከሬድዮኔ አንቴና ጋር አነካካኋት ፡፡በዚህ ዘዴ በተሻለ ጥራት ራዲዮን ማዳመጥ ቻልኩ፡፡ሁለት ቀን አልቆየሁም፡፡አንድ ሃሙስ እለት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ የቤታችን በር ተንኳኳ፡፡እንቅልፍ የማታውቀው እናቴ ጠላ የምትጠምቅበትን ትልቅ እንስራ አጥባ በወይራ እያጠነች ጓዳ ጓዳውን ትላለች፡፡በዚህ ሰዓት ቤታችን ማንም መጥቶ አያውቅም፡፡ተነስቼ በሩን ከፈትኩ፡፡ፊት ለፊቴ የተጋረጡት ሁለት ጠመንጃ የታጠቁ አብዮት ጥበቃዎች ገፋ አድርገውኝ ሲገቡ በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ፡፡ዘወር ስል እናቴ መናገር ተስኗት መሬት ላይ ተንበርክካለች፡፡እንባዬ ደረቀ፡፡ትንፋሽ ማውጣት አልቻልኩም፡፡አብዮት ጠባቂዎቹ በቁጣ ቃል ቤታችን ጣራ ላይ የተሰቀለው አንቴና  ምን እንደሆነ ጠየቁኝ፡፡እየተንተባተብኩ ለማስረዳት ሞከርኩ፡፡በጥንቃቄ ቤታችንን ፈተሹ፡፡ሽቦውን ነቃቀሉና ያችን ብቸኛ ጓደኛዬ የሆነችውን ራዲዮም "ኤግዚቢት ናት" ብለው  ወሰዷት፡፡እናቴ እኔን እንቅ አድርጋ" ስለወላድ ብላችሁ፣ ሳያውቅ አጥፍቶ ነው፡፡ ልጄን ተውልኝ " እያለች መለመኗን ቀጥላለች፡፡እኔ በድንጋጤ እንቀጠቀጣለሁ፡፡" ከጠላት ጋር በሬድዮ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል፡፡አንቺ አታውቂም" አላት አንደኛው ባለጠመንጃ፡፡ከእንባ ጋር የተቀላቀለው የእናቴ ልመና ሲብስባቸው እኔን ትተው ራዲዮናችንን ግን ይዘው ወጡ፡፡"ለማንኛውም ሁለተኛ ምንም አይነት ጣቢያ ማዳመጥ አይቻልም!!!" የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጡኝ፡፡ባይሉኝም ከዚህ ቀን ጀምሮ ራዲዮ የለኝ..በምኔ ላዳምጥ ነው?

ያቺ ሌሊት እንቅልፍ በአይኔ ሳይዞር ያደርኩባት ሆነች፡፡በስርዓቱ ተስፋ ቆረጥኩ፡፡በወደፊት ህይወቴ ተስፋ ቆረጥኩ፡፡በመፈጠሬ ተማረርኩ፡፡ኢትዮጵያ ውስጥ በመፈጠሬ ሳይሆን ሃገሬ እንደቅኝ ገዢ በህዝቡ ላይ መጨከን በማይሰለቸው በዚያ ስርዓት ተተብትባ በመኖሯ ተናደድኩ፡፡ ተሳድጄ፣ ተሳቅቄ ፣ ደህይቼ፣ አልቅሼ፣ ፈርቼ ...እስከመቼ እኖራለሁ?አልኩ፡፡መልስ ግን አልነበረኝም፡፡እነዚያ ታጋዮች የት ይሆኑ ያሉት?የሚወስደኝ ባገኝሁና አብሬያቸው ይህንን ስርዓት በታገልኩት እላለሁ፡፡እኔና ጓደኞቼ ሁልጊዜም ተደብቀን ስለደርግ መዳከም ከውጪ ስርጭት ራዲዮም ከሰውም የሰማነውን ነገር መንሾካሾካችን አልቀረም፡፡እንደዛሬው ጋዜጣ የለ፣አማራጭ የራዲዮ ጣቢያ የለ፡፡ጆሮ እንዲሰማ የተፈረደበት አንድ ነገር ብቻ፣አፍም እንዲናገር የሚፈቀድለት አንድ ነገር ብቻ በሆነበት በዚያ ዘመን ከሹክሹክታ ውጪ ሌላ ምን አማራጭ ነበረን?ሁላችንም መርሮናል፡፡ግን አንዳች ምሬታችንን የምንወጣበት መንገድ ደግሞ አናውቅም፡፡በልጅነታችን ስለራሳችንና ተምረን በሃገራችን ስለሚኖረን ሚና ማሰብ ሲገባን ዛሬ ነገ ታፈስን እያልን በጭንቀት እንኑር?እኔማ  ይህቺ መከረኛ እናቴ ባትኖር ኖሮ ያኔ በእግሬም ቢሆን ይቺን ሃገር ጥዬ በጠፋሁ እላለሁ፡፡እንኳን ሌላ ሃገር ሲኦልም ብገባ ቅር አይለኝም ነበር፡፡ደርግ የዚያን ዘመን ወጣቶች ስደት ናፋቂ አድርጎ ያስቀራቸው በጠንካራ

ብትሩ ይቀጠቅጣቸው ስለነበር ነው፡፡ከኔ በፊት የነበረው ትውልድ እየተጨፈጨፈ አለቀ፡፡የኔ ትውልድ ደግሞ መንገዱ ታጥሮበት የይስሙላ ኑሮ ይመራል፣ከእጅ አይሻል ዶማ፡፡ይኸው ዛሬ ራዲዮ ማዳመጥ እንኳን ተከለከልኩ፡፡ፈራሁት ብቻ አይደለም፣ደርግን ጠላሁት ማለት ይቀለኛል፡፡

ኋላ ላይ አንድ አብዮት ጥበቃ በአማላጅ ራዲዮኔን ከእስር አስለቅቀው ከከባድ ማስጠንቀቂያ ጋር ይዘውልኝ መጡ፡፡ለዚህ ውለታቸው ብለው ነው መሰለኝ ለብዙ ወራት የእናቴን ጠላ ያለክፍያ ሲጠጡ ኖሩ፡፡እንደውም ሰው ሁሉ ጋብዘው አይከፍሉም ነበር፡፡ይህቺ ራዲዮ ታዲያ ከአመት በኋላ አንድ ቀን ማለዳ ህይወቴን የለወጠውን ዜና ነገረችኝ፡፡

የ10ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ ፡፡መጨረሻዬ ምን ሊሆን እንደሚችል እያሰብኩ እዋትት ነበር፡፡እናቴ ዛሬም ከጠላ መሸጥና ከልፋት አልወጣችም፡፡እኔም ባለችኝ አቅም ሰርቼ ልረዳት አልቻልኩም፡፡ቢያንስ ራሴን ከጫንቃዋ ላይ አላወረድኩላትም፡፡ፀረ ወጣት የሆነው ያ ስርዓት ''ሁሉም ነገር ወደጦር ግንባር'' ብሎ እያወጀ በነበረበት በዚያ ጊዜ ሰርቶ መኖር ቀርቶ ወጥቶ መግባት እንኳን እድል ነበር፡፡ 17 ዓመት ሙሉ ተቀምጦ ከኃይለሥላሴ በተረከበው አንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ሌላ ሳይጨምር የኖረው ደርግ 12ኛ ክፍል ውጤት ያልመጣላቸውን የሰፈሬን ልጆች ''የሰፈር አውደልዳይ'' አድርጎ ሲያስቀራቸው አይቻለሁ፡፡እናት ወልዳ ታሳድጋለች፣እሱ እንደደለበ ከብት ወጣቱን ጦር ሜዳ ወስዶ ይማግዳል፡፡የኔ ነገርም ያሳስበኝ ይዟል፡፡አማራጭ ትምህርት የለ፣የሙያ ስልጠና የለ፣የግል ኮሌጅ የለ፣በቃ ህይወት የሆነ ቦታ ላይ ቀጥ ብላ ዑደቷን የምታቆምበት ጊዜ ላይ ነበር የምኖረው፡፡መጨረሻዬ ወይ በግድ ወታደር መሆን፣አለበለዚያም አገር ጥሎ መሰደድ ነው፡፡ሁለቱም ግን ለዚህች ደሃ እናቴ ከመሞት ያላነሰ ሃዘን የሚፈጥሩ ነገሮች ናቸው፡፡እንግዲህ የት ይገባል?ቀን የሚያመጣውን እየጠበቁ መዝለቅ እንጂ ምን ይደረጋል?እላለሁ ለራሴ፣ተስፋ ስቆርጥ ፡፡በዚህ መሃል ነው ያቺ ቀን የመጣችው፡፡

**ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም**

ማታ እንደወትሮዬ ጥናቴን ጨርሼ ነው የተኛሁት፡፡ማለዳ ላይ ወደትምህርት ቤት እሄዳለሁ፡፡እኔና እናቴ ያገኘነውን ተቃምሰን ተመስገን ብለን ነገን ለማየት መንጋቱን እየጠበቅን ተኛን፡፡ከእንቅልፌ ስነቃ ግን አዲስ አበባ በማይታመን ወሬ ታምሳ አገኘኋት፡፡ሰው ወደስራ አልሄደም፡፡ሁሉም ተሰብስቦ የሚያወራበት ቦታ ይፈልጋል፡፡የኛ ቤት በዚህች ቀን የተመቸ ሆኖ ተገኘ፡፡ጠላ የሚጠጣውም የማይጠጣውም በጋራ ቤታችንን አጥለቀለቀው፡፡ረፋዱ ላይ ራዲዮኔ አንድ ነገር አበሰረችኝ፡፡

'' የዘመናት የህዝብ ብሶት የወለደው ጀግናው የኢህአዴግ ሰራዊት..ደርግ ሲጠቀምበት የነበረውን የአዲስ አበባ ራዲዮ ጣቢያ..ለህዝብ ጥቅም ሲል ተቆጣጥሮታል..ግንቦት 20 1983 ዓ.ም ''

ቀኑን ሙሉ ይውል የነበረው የቤታችን የጠላ ገበያ ፀሐይ ገና በቅጡ መሞቅ ሳትጀምር ተጠናቀቀ፡፡እውነት ለመናገር በስርዓቱ መውደቅ እንደኔ ደስ ያለው ያለም አልመሰለኝ፤ የታባቱ ስል የሰማችው እናቴ ተንደርድራ አፌን አፈነችው፡፡ምን ታድርግ?ፍርሃቱ እንዲህ በቀላል መች ይለቃታል?፡፡ረፈድፈድ ሲል ደርግ አውሬ አድርጎ ሲስላቸው የነበሩት ታጋዮች ምን እንደሚመስሉ ጠጋ ብዬ ማየት ፈለግኩ፡፡ከአብሮአደጎቼ ጋር ከወላጆቻችን ተደብቀን ወደአስፋልት ወጣን፡፡ለመጀመሪያ ጊዜ ጠመንጃ ከያዘ ሰው ጋር በድፍረት ፊት ለፊት የተያየሁት ያን ቀን ነው፡፡የተጎሳቆለ ፊት፣ ያጎፈረ ጸጉር ፣ምቾት የማያውቅ ሰውነት ያላቸው ታጋዮች እዚህም እዚያም ከህዝቡ ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡እኔ የማውቀው ወታደር ሲባል ሁሌ ፊቱ የማይፈታና በማንኛውም ሰዓት አይንህ ቀላ ብሎ ያሻውን

ማድረግ የሚችል፣ የወታደር አለቃ ሲባል ደግሞ ቦርጩን አንዘርጥጦ በወታደራዊ መኪናው ወዲህ ወዲያ እያለ በሚያየው ሁሉ ላይ ፍርሃትን የሚያነግሰውን ነው፡፡ትምህርት ቤቴ ሳለሁ ከህግ በላይ የነበሩት የወታደር ባለሥልጣን ልጆች ሽጉጥ እየያዙ ስንቱን መምህር ያስደነግጡትና ያዋርዱት እንደነበር አውቃለሁ፡፡የደርግ ፖሊሶች ቆመጥ ሲይዙ እንኳን እንደዚያ እንደማንፈራቸው ዛሬ ደፍረቱን ማን አንደሰጠን እንጃ እነዚህን ታጋዮች ቀረብናቸው፡፡ከአንዱ ታጋይ ጋር ብዙ አወራንና በመሃል የታጠቅከውን መሳሪያ ልንካው ስለው የጥይት ካርታውን አውጥቶ ለጥቂት ደቂቃ እንዳነግተው አደረገኝ፡፡ደስ አለኝ፡፡ደግሞም ገረመኝ፡፡"ታዲያ ደርግ አውሬ የሚለው ማንን ነበር?ራሱን እንጂ እነዚህን ታጋዮችማ ሊሆን አይችልም" አልኩ፡፡

ከዛሬ ጀምሮ እኔና ተሰብስበን ለማውራት ቀርቶ በአንድ ላይ ለመታየት እንኳን እንሳቀቅ የነበርነው የሰፈሬ ልጆች ነጻ ወጣን፡፡ለምን እንደሆነ እንጃ እነዚህን ታጋዮች ድሮ እናውቃቸው እንደነበር ሁሉ በጣም ቀረብናቸው፣አመንናቸው፡፡ከተማውን እያሰስን ክፍት በነበረው የታችኛው ቤተመንግስት በር ወደውስጥ ስንገባ ሁሉ አልፈራንም፡፡በአጠገቡ ስናልፍ ዘወር ብለን ያየን እንደሁ ጉዳችን ነበር ያኔ፡፡ኋላ ላይ አንዲት ሴት ታጋይ ድንገት መጥታ በዚህ ሰዓት የደርግ ወታደሮች በነበሩባቸው ቦታዎች ውስጥ መገኘት አደጋ ሊፈጥርብን እንደሚችል ነግራ በፍቅር ሸኘችን፡፡

እኔና የኔ ትውልድ የነበረን ከፍተኛ የነጻነት ፍላጎት ታስሮ እንደተፈታ ጥጃ ነበር ያደረገን፡፡ታጋዮቹን በጥያቄ ቀኑን ሙሉ አደረቅናቸው፡፡ሳይታክቱ መልስ ሰጡን፡፡በህይወቴ እንደዚያን ቀን የለውጥ አየር ነፍሶብኝ፣የነጻነት ስሜት ተጋብቶብኝ አያውቅም፡፡ለመጀመሪያ ጊዜ መጪው ዘመኔ ብሩህ ሆኖ ታየኝ፡፡በቃ ያ ሁሉ ነገር አልፏል አልኩ፡፡ነገን በተስፋ አለምኳት፡፡

**ድህረ 1983 ዓ.ም**

ተስፋዬ እውን ነበር፡፡እንደዚያ የምጠላው የፖለቲካ ትምህርት ቀረልኝ፡፡አሁን በተረጋጋ አዕምሮ ለውጤት አልሜ መማር ጀመርኩ፡፡ቁመቴ ጨመረ ብሎ መፍራት የለ፣ የግዳጅ ውትድርና የህይወቴን አንጓ ይሰብረዋል ብሎ መጨነቅ የለ፣ከኔ የሚጠበቀው መማር ትምህርቴንም በነጻነትና በክፍት አዕምሮ መከታተል ብቻ ነበር ፡፡12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ስወስድ እፎይታ ተሰማኝ፡፡ባልፍ ዩኒቨርሲቲ፣ባላልፍ ደግሞ የሆነ ነገር ከመስራት የሚያግደኝ ነገር የለም፡፡ይህቺ አዲስ ሃገር እንደኔ ራዕይ በሰነቁና ከጦርነት ማግዶ በተረፉ ወጣቶቿ አንድ ቦታ መድረሷ እንደሁ አይቀርም እላለሁ፡፡ተስፋ ሲለመልም ኑሮም ቀለል እያለ መጣ፡፡

በሃገሪቱ የታወጀው ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፡ከቦታ ቦታ ያለገደብ የመንቀሳቀስ ነጻነትና የመደራጀት መብቶች ተለጉሞ የኖረውን አፍ አፍታቱት፡፡ታስሮ የኖረውን እግር አንቀሳቀሱት፣የፍራቻ ቡልኮን ከየሰዉ ላይ ገፈፉት፡፡እኔና ጓደኞቼ በዚህ ነጻ ስሜት ውስጥ ሆነን ነው ትምህርታችንን ያጠናቀቅነው፡፡ለዘመቻ ሊመለምሉን ሲሉ ከትምህርት ቤት ጠፍተን ወደቤታችን በመግባት እንዳልተሸሸግንና ዳግም ወደዚያ ለመመለስ እንዳልፈራን ሁሉ ዛሬ በሃገር ተረካቢነትና በዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳቦች ዙሪያ ለመወያየት ከትምህርት ቤት ግቢ የማንወጣ ልጆች ሆነን ነው 12ኛ ክፍልን የጨረስነው፡፡

ከብዙ ጓደኞቼ መሃል ተሳክቶልኝ ዩኒቨርሲቲ ገባሁ፡፡ያልተሳካላቸው ደግሞ አዳዲስ በተከፈቱ የግል ትምህርት ተቋማት ገብተው መማር ቻሉ፡፡አማራጮች ሰፊ ስለነበሩ ማንኛችንም 12ኛ ክፍል መውደቅ የአለም መጨረሻ ነው ብለን አልሰጋንም፡፡በውጤቱም

የደሃ ቤተሰቦቻችንን ልፋት ለመመለስ፣በዜግነታችንም ይህቺ ሃገር ከኛ የምትፈልገውን ለማድረግ ቻልን፡፡እኔ በበኩሌ እናቴን ጧሪ ለመሆን ችያለሁ፡፡ዛሬ ደስተኛ ሆና የውለታዋን እያገኘች ነው፡፡በእውቀቴም ሃገሬ ከኔ የምትፈልገውን እያበረከትኩ ነው፡፡ያን ዘመን ቂጭ ብለን ከእናቴ ጋር ስናስበው ከኔ በላይ የሚያንገፈግፋት እሷ ናት፡፡ሁልጊዜም ከማትለይበት ቤተክርስቲያን ስትመለስ" ተመስገን !!ጨለማውን ዘመን በብርሃን ተክተህ ለዚህ ያደረስከን ጌታ ምን ይሳንሃል " ትላለች፡፡

ዛሬ ትልቅ ሰው ሆኛለሁ፡፡ደርግ ሲወድቅ ከነበርኩበት እድሜዬ ላይ 20 ዓመታትን ጨምሬያለሁ፡፡ኖርኩ የምለውም እነዚህን አመታት ብቻ ነው፡፡ከዚያ በፊት እናቴ ዘወትር እንደምትለው እውነትም ጨለማ ዘመን ላይ ነበር የኖርነው፡፡ለኔ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ግርዶሽ የነበረው ዘመን ሲገፈፍ የታዩት ለውጦች እንዲህ በቀላል ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም፡፡እኔ እያልኩ የማወራው የእኔ ታሪክ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት ታሪክ ነበር ብዬ ስለማስብ ነው፡፡ዛሬ ላለው ለዚህ ዘመን ወጣት ብዙ አማራጮች ቀርበዋል፡፡ማሰብ የተሳነው ደርግ የተማረ ኃይልን ሲቀጠቅጥ ኖሮ ሃገሪቱን "አሜን ብቻ በሚል ያልተማረ ህዝብ" ለመሙላት አዲስ አበባን በአንድ ዩኒቨርሲቲ አስቀርቷት ነበር፡፡ዛሬ ግን የተማረ ኃይል የዚህችን ሃገር መሪ መዘወሩ ግድ መሆኑን የሚያምነው መንግስት በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን በ20 ዓመታት ውስጥ ገንብቶ ለወጣቱ መጠነ ሰፊ እድል ከፍቶለታል፡፡በየክልሉ ያሉ የቴክኒክና የሙያ ኮሌጆች ወደቀለም ትምህርት ለመዝለቅ አቅም ያነሳቸውን ወጣቶች በተለያየ ሙያ በማሰልጠን አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ያደረጉት ጥረት ተሳክቷል፡፡መንግስት በሚከተለው ፖሊሲ የግል ባለሃብቶች በትምህርት ዘርፉ ላይ መዋዕለንዋያቸውን ስራ ላይ በማዋላቸው ሁሉም እንደየፍላጎቱ የእውቀትን ገበታ የሚታደምባት ሃገር ተፈጥራለች፡፡ዛሬ እንደዚያ ጨለማ ዘመን ብሄራዊ መልቀቂያ ፈተናን አለማለፍ ማለት የእድልና የህይወት መጨረሻ ማለት አይደለም፡፡

አነስተኛና ጥቃቅን ዘርፍ ደግሞ በሙያ ስራ ላይ ተሰማርቶ ራሱንና ሃገሩን መጥቀም ለሚፈልግ ዜጋ ሰፊ አማራጮችን ይዞ መጥቷል፡፡ዛሬ ከምንም ተነስተው ስራ እየሰሩ የራሳቸው ጌታ የሆኑ ሚሊየነር ወጣቶች ስንቶች ናቸው?የራሳቸው እመቤት መሆን የቻሉ ሴቶችና እናቶችስ ስንት ናቸው? በዚህ ዘመን ተስፋ አልባ የሚባል ሰው የለም፡፡መስራት እስከቻለ አማራጮቹ ብዙ ናቸው፡፡መማር እስከቻለ በራቸውን ክፍት አድርገው የሚጠብቁ ትምህርት ቤቶች የትየለሌ ናቸው፡፡ብቻ ማንም ሰው መሆን የሚፈልገውን ለመሆን የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ባለራዕይ ሆኖ መገኘት ብቻ ነው፡፡የማይቻል ነገር የለም፡፡

ለእኔ ግንቦት 20 የልደት ቀኔ ናት፡፡በአካል ሳይሆን በመንፈስ የተወለድኩባት ቀኔ፡፡ይህቺ ቀን ለመላው ኢትዮጵያዊ ይዛው የመጣችው ለውጥ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡በትምህርት፣በጤና፣በመሰረተ ልማት ግንባታ፣በስራ ፈጠራ፣በማህበራዊና በፖለቲካዊ መብቶች ወዘተ የተገኙት ውጤቶች የዚህች የድል ቀን ፍሬዎች ናቸው፡፡እኔንና መሰሎቼን ከተስፋ መቁረጥ አውጥቶ በትግላችን ልንደርስ የምንፈልግበት ደረጃ ላይ ያደረሰንን እድል ያገኘነው በግንቦት ሃያ ነጻነትና ከዚያ በኋላ በተደረጉ የልማት ትግሎች በተመዘገቡ ድሎች ነው፡፡

ይህቺን ሃገር ከነበረችበት የድህነትና የኋላ ቀርነት አረንቋ አንዳች እንኳን ፈቀቅ ሳያደርግ እድሜውን ሙሉ ጦር በመገንባት ያሳለፈው ወታደራዊ መንግስት የጭቁኑን ህዝብ ድምጽ ነጥቆ ስልጣን ላይ ፊጥ ከማለትና መልሶ የህዝብ ጩኸትን ከመርገጥ ውጪ ይህ ነው ተብሎ የሚቆጠር ለውጥ አላመጣም፡፡17 ዓመታት እንደዋዛ ባክነዋል፡፡እንኳን ሊጨመር ያለውም እየተቀነሰ ሃገሪቱ ህልውናዋ አጠያያቂ ሲሆን ነው ቆራጥ የህዝብ ልጆች በኢህአዴግ መሪነት 17 ዓመት ታግለው ለዚህች ሃገር የደረሱላት፡፡ከዚያች ድል ከተበሰረባት የግንቦት 20 ማለዳ በኋላ የነበሩት 20 ዓመታት ደግሞ በማንም ሰው ሀይወት ውስጥ ለውጥ አስመዝግበው አልፈዋል፡፡የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ካወጣቸው

የሚሊኒየም ግቦች ውስጥ በተለይም በትምህርትና በጤና መስክ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ስኬት ማስመዝገብና ግቦቹን ማሳካት እንደምትችል ከወዲሁ ተተንብዮላታል፡፡አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋንን ሙሉ በሙሉ በመላው ሃገሪቱ ለማዳረስ የተያዘው እቅድ የተሳካ የሚባል ውጤት አስገኝቷል፡፡ልጆች በየአካባቢያቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ በማድረግ ቋንቋቸውን እንዲያሳድጉ፣በተቀላጠፈ ሁኔታ እውቀት እንዲገበዩ እንዲሁም ባህላቸውንና እሴታቸውን ጠብቀው በዚህች ሃገር ግንባታ ላይ የጋራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተደረጉት ጥረቶች ውጤት አሳይተዋል፡፡መንግስት ማንነቱን የሚያከብርና በማንነቱ ኮርቶ አንዲት ኢትዮጵያን በጋራ መፈቃቀድ የሚገነባ ህብረብሄራዊ ተሳትፎ ያለው ዜጋ ለማፍራት ያደረገው ጥረትና የወጠናቸው እቅዶች ተሳክተውለታል፡፡ኢትዮጵያ ዛሬ በብሄሮች መፈቃቀድ የገነባችው የፌዴራሊዝም ስርዓቷ ለሌሎች ሃገራት መማርያና ልምድ መለዋወጫ መሆን መቻሉን እያየን ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለማግኘት የትውልድ አካባቢን ጥሎ መሄድ ፣በሌለ አቅም ቤት ተከራይቶ በችግር መማር በብዙ የሃገራችን ገጠራማ አካባቢዎች የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ያለፉበት እጣ ፈንታ ነበር፡፡"ጥረትና ስኬት" በሚል ርዕስ ታህሳስ 30 ቀን 2003 በታተመና የአንዲት ኢትዮጵያዊት ባለሃብትን የህይወትና የስራ ታሪክ በሚዳስስ መጽሄት ያነበብኩት ነገር ለዚህ ማስረጃ ይሆነኛል፡፡ሴትየዋ በጥረታቸው ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ አሉ ከሚባሉት ባለሃብቶች ጋር ቢደመሩም ልጅነታቸው ያለፈው ግን በትውልድ አካባቢያቸው ጉራጌ ዞን ውስጥ ለትምህርትና ለእውቀት ሲኳትኑ ነው፡፡በዚያ ዘመን እሳቸውና የዚያ ዘመን ጓደኞቻቸው አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማግኘት በቀን ከ6 ሰዓት በላይ መጓዝ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ሁለተኛ ደረጃ ለመማር ደግሞ የትውልድ ቀያቸውን ጥለው የአንድ ቀን መንገድ ተጉዘው በማያውቁት ስፍራ ተከራይተው መኖር ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡በዚህ መሃል በአቅም ማነስ፣በህመም፣በተለያዩ አደጋዎች ትምህርታቸውን ዳር ማድረስ ያልቻሉ ብዙ ጓደኞቻቸውን ሲያስታውሱ "ቁጭት ይሰማኛል" ይላሉ፡፡ዛሬ በትውልድ ቀያቸው ያለው የትምህርት ቤት እጦት ተወግዶ ከአንድም ስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህት ቤቶች፣እንዲሁም አንድ የቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋም ተገንብቶ ሲያዩ የተናገሩት ነገር የማይረሳ ነው፡፡" የዚህ ዘመን ወጣቶች እድለኞች ናችሁ፡፡እኛ በልፋት ተምረን እዚህ ደርሰናል፡፡እናንተ ደግሞ ደጃችሁ ላይ የቀረበላችሁን እድል ተጠቅማችሁ እኛ ከደረስንበት በላይ ስኬት ልታስመዘግቡ ይገባል፡፡ይህቺ ሃገር አንድ ቀን ከፍ ያለ መንበር ላይ ትቀመጣለች፡፡ለዚህ ኃላፊነቱ የተጣለው ደግሞ እናንተ ላይ ነው፡፡የአሁኑ ስራችሁ ሊሆን የሚገባው ጠንክሮ መማር ብቻ ነው፡፡"እኚህ ኢትዮጵያዊ ያለፉበትን የትምህርት እጦት ዘመን ብዙዎች አልፈውበታል፡፡ዛሬ ግን እሳቸው እንዳሉት ሁሉም ነገር ተቀይሯል፡፡ግንቦት ሃያ የዚህ ድል ብስራት የተነገረባት ቀን ናት፡፡ልማታዊ አስተሳሰብ ይዞ የተነሳው ልማታዊ መንግስት ለዚህች ሃገር ብልጽግና መሰረቱ እውቀት መሆኑን ይረዳልና ለትምህርት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑ የሚታይ ሃቅ ነው፡፡

በጤና በኩልም ተመሳሳይ ነው፡፡በመላው ሃገሪቱ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ በማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን በመቅረጽና መከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ያለፉት 20 ዓመታት የተሳኩ ውጤቶች የታዩባቸው ነበሩ ፡፡ከገጠር እስከከተማ የተቋቋሙት የጤና ተቋማትና ኬላዎች በዚሁ ልክ ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት የሃገሪቱ ዜጎች ጤናቸው ተጠብቆ አምራች እንዲሆኑ አስችሏል፡፡የእናቶችና የህጻናትን ሞት ለመቀነስ የተደረጉት ጥረቶች የተባበሩት መንግስታትን አድናቆት አስገኝተዋል፡፡የኤች አይቪ ኤድስን ስርጭት በመቀነስ መከላከል ላይ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብም የዚሁ አካል ነው፡፡ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውጪ ሪፈራል ሆስፒታል ያልነበረበት ሃገር አሁን በተለያዩ ክልሎች የግልና የመንግስት የህክምና ተቋማትን በመገንባት ችግሮችን ለመቅረፍ ባለፉት 20 ዓመታት ተጨባጭ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የግሉ ባለሃብት በህክምና ዘርፍ ላይ እንዲሰማራ በተደረገለት ድጋፍና

እገዛም ዛሬ በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል የተለያዩ ባለሃብቶች የገነቧቸው የጤና ተቋማት አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ይህን ሳስብ ከ20 ዓመታት በፊት የነበርንበትን ሁኔታ በአይነ ህሊናዬ ድቅን ይላል፡፡በአካባቢያችን ወዳለው ጤና ጣቢያ ለመታከም ስንሄድ ወረፋ የምንይዘው ከኬሊቱ 9 ሰዓት መሆኑን ሳስታውስ፣ በተለይ እናቴ ስትታመም የምወስዳት ቦታ ግራ ሲገባኝ አሳልፋቸው የነበሩትን የሃዘን ቀናቶች አስባቸዋለሁ፡፡አይ ጊዜ !! እላለሁ፡፡ ባያልፍ ኖሮ እንዴት ክፉ ነበር?

ሌላው ሁልጊዜም ግርም የሚለኝ በግብርና ዘርፍ የተገኙት ውጤቶች ናቸው፡፡እውነት ለመናገር ያኔ የነበርን ልጆች አላዋቂ ሰውን የምንገልጸው "ገበሬ" ብለን በመወረፍ ነበር፡፡ምን እናድርግ፣ስርዓቱ ያወረሰን " ገበሬ ምን ዋጋ አለው " የሚል አስተሳሰብ ውጤቶች ነበርን፡፡"ሆ በል ገበሬ ባንተ ነው ማማሬ " የሚለው ዘፈን ሽንገላ ብቻ ነበር፡፡ደርግ የቀበሌ ኪነትን አቋቁሞ ለተራ ፕሮፓጋንዳና ዕድሜ ማራዘሚያ ሲጠቀምበት ስንቱን በዘፈን ሸንግሎ እንደነበር የቀድሞዎቹን "የአብዮት ዘፈኖች" የሚያስታወስ ሁሉ የማይረሳው ሃቅ ነው፡፡ገበሬው ዓመት ለፍቶ ከሶሰት ወር በላይ ጠግቦ ሳይበላ ሁልጊዜም ለችግር የሚጋለጥ የነበረበት ዘመን ፣ያም አልበቃ ብሎ ሞፈርህን ሰቅለህ ዝመት እየተባለ በሚሊሺያ ሰራዊት ውስጥ ሲሰገሰግና ሲማገድ የነበረበት ጊዜ ማለፉን እንደተዓምር ነው የማየው፡፡ዛሬ ገበሬ መድረክ አግኝቶ ሲናገርና ሲሸለም ማየቴ፣ሚሊየነር ገበሬ ማፍራት መቻሉን በየአጋጣሚው በአይኔ አይቼ ለራሴ መመስከሬ፣በአጠቃላይ ለገበሬው በተሰጠው ትኩረት የተገኙትን ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ውጤቶች መታዘብ መቻሌ" ደርግ ምን ያህል ማሰብ የተሳናቸው ሰዎች ጥርቅም ቢሆን ነው ይህን እውነት ማገናዘብ ያቃተው" ብዬ አምርሬ እንድንቀው  አድርጎኛል፡፡ ለነገሩ ደርግን የጣሉት ያመረተውን ሲቀማውና ሞፈሩን አሰቅሎ ለግዳጅ ውትድርና ሲዳርገው የኖረው ገበሬና ከአብራኩ የወጡት ጭቁን ልጆችም አይደሉ?...

ኢትዮጵያ በግብርና ምርት እድገት አስመዘግባ በምግብ ምርት ራሷን ችላ ከተመጽዋችነት እንድትላቀቅ ለማድረግ ቀዳሚው ጉዳይ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ  ማጠናከር ነው ብሎ ያመነው ኢህአዴግ እነሆ ዛሬም  ዘርፉን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ቁንጮ አድርጎታል፡፡ቀስ በቀስ በኢንዱስትሪ እስኪተካ ድረስ የሃገሪቱን ልማት በማፋጠን መሪውን እየዘወረ ያለው ግብርና ነው፡፡የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ አቅጣጫ ትክክለኝነቱ በተግባር የተረጋገጠ ስለመሆኑ ያለፉት 20 ዓመታት ለውጦች በቂ ምስክር ናቸው፡፡

ዛሬ ሳስበው ይገርመኛል፡፡አዲስ አበባ ውስጥ ተወልጄ ያደኩት ሰውዬ 12ኛ ክፍል እስከጨርስ ድረስ ከጓደኞቼ ጋር ትምህርት ቤት የምመላለሰው ወንዝ በእግሬ በማቋረጥ ነበር፡፡በሌላ መንገድ እንሂድ ብንል ብዙ ሰዓት ይወስድብን ነበርና፡፡ዛሬ ግን የሰፈሬ ልጆች እኔ የተማርኩበት ትምህርት ቤት ለመድረስ ዘና ብለው 20 ደቂቃ ቢወስድባቸው ነው፡፡ለዚያውም እሱ ራቀን ብለው በአቅራቢያችን ያለ ሌላ ትምህርት ቤት ነው የሚማሩት፡፡ከሰፈራችን 10 ደቂቃ ብቻ፡፡ዛሬ እንዲህ አገር ምድሩ በአስፋልት አጊጦ ሳየው ያኔ እንደመስቀል አደባባይ ያለ ዘመናዊ መንገድ በአለም ላይ የሚገነባም አይመስለኝ ነበር፡፡አንድ ሰፊ መንገድ እሱ ብቻ ነበር። ለዚያውም ደርግ በየአመቱ መስከረም ሁለት ቀን በብረት ታንክ እየገማመሰ ትርዒት እያሳየበት ጭምር ፡፡ዛሬ አየኋ!!ቅቤ ቢፈስበት የሚታፈስ የሚመስልበት አስፋልት፡፡

እውነት ለመናገር ባለፉት 20 ዓመታት ለመንገድ ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት ያስገኘውን ውጤት ተቃዋሚዎች ሳይቀሩ ያጨበጨቡለት ሃቅ ነው፡፡ከተሞችን ከከተሞች፣ክልሎችን ከክልሎች ያገናኘው መንገድ ሁሉ የተገነባው በዚህ 20 ዓመት ውስጥ ነው፡፡ደርግ ጣሊያንና ንጉሱ የሰሩትን መንገድ እንኳን በአግባቡ መያዝ ተስኖት አውራ ጎዳና ብሎ ያቋቋመውን ድርጅት ስንት ዓመት ስራ አስፈትቶ እንዳኖረው  እኮ አንረሳውም፡፡ብዙ የተባለለት

ቢሆንም እኔ በበኩሌ የተዋጣለት የመንገድና ሌሎች የግንባታ ውጤቶች  የዚህ ልማታዊ መንግስት የ20 ዓመት ጥረት ሜዳሊያዎች ናቸው እላለሁ፡፡የመንገድ ግንባታ እንቅስቃሴያችን የአፍሪካ ሃገራት እንኳን የተደነቁበትና ልምዳችሁን አካፍሉን ብለው ጥያቄ ያቀረቡበት ዘርፍ ነው፡፡

ያኔ ከኛ ጋር የማይኖረው አባቴ ስልክ ሲደውል ለማነጋገር ከእናቴ ጋር ወዲያ ማዶ የሚገኝ አንድ ሰፈር የምንሄደው በቀጠሮ ነው፡፡ምናልባት የሱን የስልክ ጥሪ ጥበቃ ግማሽ ቀን ልንፈጅም  እንችላለን፡፡ያም ሆኖ አምስት ደቂቃ ማነጋገር ለወጪ ስለሚዳርግ ነው መሰለኝ ሳንጠጋገብ ነው ስልኩ የሚቋረጠው፡፡1983 ዓ.ም ድረስ እኛ ቤትም ሆነ ሰፈራችን ውስጥ ስልክ ያለው ሰው አልነበረም፡፡ዛሬስ?ስምንት ልጆች ያላቸው ጎረቤታችን እንኳን በቤታቸው ውስጥ 8 ሞባይል ስልክ አለ፡፡እናቴ ራሷ ሞባይል አላት እኮ!!!የቤቱን ስልክ ተውትና ማለቴ ነው፡፡የቴሌኮሙኒኬሽን ዝርጋታ የተራራቁ ሰዎችን አንድ ላይ የሚያኖራቸው ያህል ሆነዋል፡፡የትኛውም ርቀት ላይ የሚኖር ሰውን በቀላሉ ማግኘት ችለናል፡፡በእያንዳንዱ ደቂቃ ያሻኝን ሰው ደውዬ ድምጹን መስማት ከቻልኩ አብሬው ኖርኩ ማለትም አይደል?ባለፉት 20 ዓመታት በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የተመዘገበው ፈጣን እድገትም የህዝቡን ህይወት ቀላል አድርጎታል፡፡የመገናኛ አውታሮች መስፋፋት ለኢኮኖሚው እድገት መፋጠን ጉልህ ድርሻም ተጫውቷል፡፡እንግዲህ የግንቦት 20 ፍሬ ስንቱ ተጠቅሶ ይቻላል?

ዛሬ

ከዚያች የግንቦት 20 ማለዳ በኋላ ዳግም የተወለድኩ ያህል እንዲሰማኝና "ግንቦት 20 ልደቴ ነው" ብዬ እንዳስብ ያደረገኝ ነገር እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ ይኸው ነው፡፡ልዘርዝረው ብል በእኔ በአንዱ ግለሰብ ህይወት ላይ ብቻ ያለፉት 20 ዓመታት ያስቀመጡትን አሻራ አውርቼ አልዘልቀውም፡፡ብዙሃኑ የኢትጵያ ወጣት ደረጃው ይለያይ እንጂ የኔኑ አይነት ህይወት ያሳለፈ ስለመሆኑ አንዳች ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ለዚህም ነው ለሚሰራ እንጂ ለሚያወራ አካል ጆሮዬን የማልሰጠው፡፡ለሚታገልና ለለውጥ ለሚተጋ ፓርቲ እንጂ በራሱ ስንክሳር ለሚተራመስ አጀንዳ ቢስ ለአፍታም ልቤ ደንገጥ የማይለው፡፡ይህቺን ሃገር ወሬ ሳይሆን ተጨባጭ ስራ ነው የሚያሳድጋት፡፡እስከማውቀውና እስከማምነው ድረስ የዚህ መንግስት አጀንዳ ሶስት ምሰሶዎች ላይ የታሰረ ነው፡፡ዴሞክራሲ ፣ልማት፣ሰላም፣ከዚህ ውጪ ለህዝብ ምን የሚጠቅም ነገር አለ?ሌላው ቀርቶ ባለፉት 20 ዓመታት ሃገሪቱ በተጨባጭ የደረሰችበትን የኃይል አቅርቦት አቅም የመዘነ ሰው፣በንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አሁን ያለንበትን ደረጃ የተረዳ ሰው..ኧረ በሌሎችም ብዙ ዘርፎች ይህቺ ሃገር ያሳየችውን ከፍተኛ መሻሻልና እድገት የተረዳ ሰው   ይህ መንግስት ለቆመለት ልማት እውን መሆን ሲተጋ ለአፍታ እንኳን እንቅልፍ የማይወስደው መሆኑን ያውቃል፡፡መሪው ፓርቲ ኢህአዴግ ጓዶች የተሰውለት ዓላማ ተግባራዊ መሆኑን ሳያረጋግጥ እረፍት እንደማይሰማውም ይረዳል፡፡ያ! ለዚህች ቀን መምጣት ሲታገል የተሰዋ ትውልድ አሁንም አደራው በዚህኛው ትውልድ ጫንቃ ላይ መሆኑን ግን ለአፍታም መዘንጋት የለብንም፡፡

ቆራጥ አላማ አንግቦ ደርግን የሚያህል ግዙፍ ተራራ ከስሩ ገርስሶ  የጣለው ትውልድ አሁን ላለነው የዚህኛው ዘመን ኗሪዎች ታላቅ የታሪክ እዳ ጥሎብን ነው ያለፈው፡፡አሁን በተራችን የእርሱን ጋሻ አንስተን ድህነትን የሚያህል ግዙፍ ጠላት ማንኮታኮትን ከእኛ ይጠብቃል፡፡ያ ታጋይ ትውልድ  አይቻልም የተባለውን እንደሚቻል ለማሳወቅ በደሙና በአጥንቱ ታሪክ ጽፎ በማስነበብ የአላማ ጽናቱን አሳይቶናል፡፡በኋላ ቀር መሳሪያ ዘመናዊ ታንክና ጀት የታጠቀውን የአፍሪካ ግዙፍ ወታደራዊ ኃይል ገጥሜ አሸንፋለሁ ብሎ መነሳት ያኔም ሆነ አሁን ሲታሰብ የማይታመን ነገር ቢመስልም በተግባር ግን ሆኖ አይተነዋል፡፡በውጤቱም ባለዓላማው ቆራጥ ትውልድ አሸንፎ ይህቺን ሃገር ከአምባገነንነት ቀንበር ነጻ

አውጥቶልናል፡፡ይህንን ድል በእጃችን ያስጨበጠን ታጋይ  እኔ እንደሚገባኝ ትግሉን ያካሄደው ስፖንጅ ፍራሽ ላይ ተኝቶና የላመና የጣመ በልቶ አይደለም፡፡ድንጋይ ተንተርሶ፣ቆንጥር ስር ተኝቶ ፣ከረሃብ ጋር እየታገለ አንጀቱን አስሮ፣ውሃ ጥምን ተቋቁሞ፣ጥይት በጆሮው እያፏጨበት ብርድና ሃሩር እየተፈራረቁበት… ያንን ሁሉ ችሎ ነው፡፡ከዚያም ሲያልፍ ቆስሎና ህይወቱን ሰውቶ ነው፡፡ይህን  ሁሉ ሰቆቃና ስቃይ ያሳለፈው የአርባ ቀን እድሉ  ስለነበረ አይደለም፡፡የተነሳለት አላማ ግብ እንዲመታ በመሻት እንጂ፡፡እንደዚያ ባይሆንማ ኖሮ በልቶ መኖር እየተቻለ… ዛሬን ውሎ ማደር እየተቻለ… ማን ስለምን ብሎ ይሞታል?...ለማንስ ብሎ ይሰቃያል?...ታዲያ ያ! ትውልድ ለኛ ባለውለታችን አይደለምን?የነዚያ ታጋዮች ደም ለእኛ ከነጻነትና ከሰላም ባሻገር ያወረሰን ያልከፈልነው እዳ የለምን?...አለ…ገና ያልተከፈለ ውለታማ አለ!!!

ይህቺ ሃገር ከድህነት ተላቅቃ ህዝቧም ከእጅ ወደአፍ ኑሮውን አሸንፎ የኖረ እለት፣የምግብ ተመጽዋችነት ያስደፋውን አንገት ቀና አድርጎና ራሱን ችሎ መራመድ የጀመረ እለት ፣ያኔ ነው ያ ! ታጋይ ጀግና ጥሎብን ያለፈው አደራ የሚፈጸመው..እዳው የሚከፈለው፡፡ባለራዕይ ሆነን የይቻላል መርህን አንግበን የተነሳን እለት፣በተባበረ ድምጽ ለዚህች ሃገር ዳግም ትንሳኤና ህዳሴ የዘመርን እለት ፣በጋራ ክንድ ድህነትን ደምስሰን ደህና ሰንብት ያልነው እለት…ያኔ ነው አደራ የጠበቅነው፡፡

በዚያ ትውልድ የህይወት መስዋዕትነት የተረከብናት ኢትዮጵያ ዛሬ ከእኛ ደማችንን አትፈልግም፣ወዛችንንና ላባችንን እንጂ፡፡ሰርተን እንድናሻሽላት ፣ተግተን ከድህነት አረንቋ እንድናወጣት፣መካከለኛ ገቢ ..ከዚያም ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ አሰልፈን የቀደመ ክብሯን እንድናስመልስላት ነው የምትሻው፡፡ በተለጠፈባት የረሃብና የማጣት መገለጫነት ስም ሳቢያ ልጆቿ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብለው መናገርን የማያፍሩበት ጊዜ እንዲመጣላት፣ያለፈ  ታላቅ ስሟ ትንሳኤ እንዲያገኝ ብቻ ነው የምትሻው፡፡በርግጥ ይኼ በጸሎት ብቻ የሚሆን ጉዳይ አይደለም፡፡ጠንክሮ መስራትን፣ሌት ተቀን መልፋትን፣ከመንግስት ጋር ተባብሮ በልማት ላይ ያልተቋረጠ ተሳትፎ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

ያለፈው ትውልድ ይህቺን ሃገር ሲያስረክበን ለዓላማው መሳካት ሲል በፈንጂ ላይ ተንከባልሎ ህይወቱን በፍቃደኝነት ሰውቶ ጭምር ነው፡፡እልህ አስጨራሹን ትግል እስከመጨረሻው በመወጣት አሸናፊነቱን ያረጋገጠው ትውልድ ለእኛ ያወረሰን ታላቅ ትምህርት ቢኖር "ይቻላል" ብሎ የተነሳን አካል አንዳችም እንቅፋት እንደማያቆመው ነው፡፡ኢትዮጵያ ደሃ ሃገር ሆና ኖራለች፡፡ድህነታችን እድላችን አይደለም፡፡መለያችን ግን ሆኗል፡፡ድህነታችን የማንጋፋው ባላጋራችን አይደለም፡፡ገፍቶ በዓለም ፊት ምጽዋት ጠባቂ አደርጎን ግን ኖሯል፡፡ያ ትውልድ ለእኛ የነገረን ቁምነገርና ያወረሰን ወኔ  "ቁጭት" ነው፡፡ለምን ብለን እንድንጠይቅ ነው፡፡ያን ካደረግን ነቅለን የማንጥለው ችግር፣ከመንገዳችን ገፍተን የማናስለቅቀው የድህነት ጋሬጣ የለም፡፡ ከዚህ በኋላም መንገዳችን  ቀና ፣ጉዟችንም ፈጣን ይሆናል፡፡ለዚህች ቀን ላደረሱን ሰማዕታት አሁንም ክብር ይሁን፡፡

---END---